# የአገራዊ ራዕይ አልባነት ጉዞ እስከ መቼ?

21 January 2018
በፀጋዝአብ ለምለም ተስፋይ

ዓለም ከሥልጣን ፖለቲካ ወደ ፖለቲካ ተሻግሮ፣ ስለታሪክ ከመነታረክ ወጥቶ ታሪክ ስለመሥራት በሚታገልበት፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ሐሳቦች ወጥቶ እጅግ ወደ ላቀና ውስብስብ ሐሳብ በገባበት፣ ከጓዳ ፖለቲካ ወደ አደባባይ ፖለቲካ፣ ከድንበር ተሻግሮ በዓለም አቀፋዊነት በሚተጋበት እኛ ከከባቢያዊነት ወደ መንደርተኝነት ስንገሰግስ፣ ዓለም ወደ ፊት ቀን ከለሊት ሲተጋ፣ እኛ ወደ ኃላ እያሰብን ሴራ ስንጎነጉን፣ ዓለም በነገ ማዕቀፍ ሲተጋ እኛ በትናንት ማዕቀፍ ለመኖር ስንተጋ፣ ፖለቲካችን እንደ ሕፃን ልጅ በትናንሽ ነገሮች እየረካ፣ ዓለም ከመሬት ፍትጊያ ወደ ስፔስ (ህዋ) ፍትጊያ ሲገባ፣ የእኛ ግን ነገር መብላት ብቻ ቢሆን ለምን ብሎ መጠየቅ ዜጋዊ ግዴታ ሆነና ጥያቄ አነሳሁ፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን አገራዊ ራዕይ አለን? እስከ መቼ ያለ አገራዊ ራዕይ እንያዝ? ለምን?

አገራዊ ራዕይ የረዥም ጊዜ ሆኖ የሚቀመጠው በማዕቀፍ ነው፡፡ ለዚያ ማዕቀፍ የሚረዱ ግቦች፣ ዓላማዎችና ተልዕኮዎች በአንፃሩ ይኖራሉ፡፡ የአንድ አገር ራዕይ ዕምነት – አገራዊ ማዕቀፍ ነው፡፡ የአገራዊ ማዕቀፍ ምሰሶዎች በአንፃሩ አገራዊ ራዕይ በነጠላ፣ አገራዊ ግብ ለራዕዩ፣ አገራዊ ዓላማዎች ለግቡና ለራዕዩ፣ አገራዊ ተልዕኮዎች ለአገራዊ ግብና ራዕይ መሳካት ይኖራል፡፡

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ‹‹የአገሪቱ አጠቃላይ ራዕይ›› ከ 2012 እስከ 2015 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በሕዝብ ተሳትፎና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማኅበራዊ ፍትሕ የነገሠባት፣ ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ የሚል ራዕይ እንዳለ ይገለጻል፡፡

‘መካከለኛ ገቢ’ የሚለው ግብ እንጂ ራዕይ ፈጽሞ ሊሆን እንደማይችል ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ለዚያውም ከግብም ቢሆን የአጭር ጊዜ ግብ፣ ምክንያቱም ግብ በራሱ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ተብሎ ስለሚከፈል፡፡ እንደ አገር እኛ ኢትዮጵያውያን ለምንድነው መካከለኛ ገቢ ያላት አገር የምንፈልገው? የት ለመድረስ? ለምን? የሚለው ወደ ራዕይ የሚያመላክተን ሲሆን፣ ምን አገራዊ ማዕቀፍ ስላለን ነው? የሚለው ደግሞ ዓብይ የአገራዊነታችን ማሳያ አገራዊ ማዕቀፍ ይሆናል፡፡

አገራዊ ራዕያችን ምንድነው? እዚያ ለመድረስስ ምን ምን ማድረግ አለብን? በባለቤትነት ስሜት እንዴት ልንይዘው እንችላለን? አገራዊ ማዕቀፋችንን መሠረት ያደረገው እምነታችን፣ ዕውቀታችንና ተግባራችንስ ምንድነው? ማኅበራዊ ፍልስፍናችንስ ምንድነው?

የፖሊሲ ዓላማዎችና ግቦች የአገር ዓላማና ግቦች ናቸው ማለት አይደለም፡፡ የአንድ ነጠላ አገራዊ ዕቅድ ዓላማ ማለት ጠቅላላ አገራዊ ዓላማ ማለት አይደለም፡፡ ዕቅዱ የአገሪቱ በአጠቃላይ የረዥም ጊዜ ዓላማና ግብን ለማሳካት የሚረዳ አንድ መሣሪያ መሆኑ ላይ ከፍተኛ ጽንሰ ሐሳባዊ ክፍተት ከመኖሩም በላይ፣ ነጠላ ፖሊሲዎችና አገራዊ ፕሮግራሞች ላይ የሚቀመጡ ዓላማና ግቦችን የአገር ዓላማና ግብ አድርጎ የመውሰድ ከፍተኛ ጽንሰ ሐሳባዊ ክፍተት አለ፡፡

ለአብነት ‘የመጀመሪያው የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ’ በሚል በተደጋጋሚ የሚገለጸውን የወሰድን እንደሆነ፣ እንደ አገር ያልተመለሰው ዓብይ ጥያቄ ዕቅዱ ላይ ከተቀመጡ ዓላማዎችና ግቦች ባሻገር ለምንድነው አገራችን ይህ ዕቅድና ትራንስፎርሜሽን ያስፈለጋት? የት ለመድረስ? መቼ? በምን? ለምን? ስለምን? የሚሉ ዓበይት አገራዊና ሕዝባዊ ትርጉም ያላቸው አገራዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎችን ትርጉም ባለው መልኩ ምላሽ አይሰጥም፡፡

ራሱን ዕቅዱን እንኳ ብናይ ‹‹ዕቅዱ ከምንጊዜውም የላቀ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ማኅበራዊ ልማትና መልካም አስተዳደር የሚመዘገብበት፣ ከሚመዘገበው ውጤትም ሕዝቡ ፍትሐዊ በሆነ መልኩ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትና የዜጎችን ማኅበራዊ ዋስትና ለማረጋገጥ እንደሚያስችል ይታመናል፤›› በማለት ድህነትን ለማስወገድ፣ ለብልፅግና፣ ዴሞክራሲ ለማዳበር፣ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ፣ ጤናን ለማስፋፋት፣ መሠረተ ልማትን ለሁሉም ለማድረስ . . . የሚሉ ጥቅል ሐሳቦችን

ያነሳል እንጂ፣ ትርጉም ያለው አገራዊ ራዕይ፣ አገራዊ ግብ፣ አገራዊ ዓላማን ከዕቅዱ ግብ፣ ዓላማና ተልዕኮ ለይቶ አያስቀምጥም፡፡

የዕቅዱ ግብ፣ ዓላማና ተልዕኮ ማለት የአገር ግብ፣ ዓላማና ተልዕኮ ማለት አይደለም፡፡ ዕቅዱ ራሱ የአገራችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ አንድ አካል ብቻ ተደርጎ ነው መወሰድ ያለበት፡፡ አገራችን ሳትሆን የዕቅዱ አካል – ዕቅዱ ነው የአገራችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ አንድ አካል መሆን ያለበት፣ ሊሆንም የሚችለው፡፡

በፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ላይ የፖሊሲና ፕሮግራም ዓላማ፣ ግብና ተልዕኮ መገለጽ አገራዊ ራዕይ፣ አገራዊ ግብ፣ አገራዊ ዓላማ አለን አያስብልም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ጥቅል ከመሆናቸውም ባሻገር እንኳንስ እንደ መንግሥት እንደ ግለሰብ እንኳ መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳባዊ ጉድለት ያለባቸው በመሆኑ ነው፡፡

ይህም ክፍተት በዋናነት ለምን? በምን? ስለምን? የሚል ሕዝባዊና አገራዊ ትርጉም ያለው ጥያቄን ትርጉም ባለው መልኩ የማይመልስ መሆኑ ነው፡፡ ዴሞክራሲ፣ ፍትሕ፣ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት፣ ተደራሽነት፣ ሰላም፣ ብልፅግና፣ መልካም አስተዳዳር፣ . . . ለምን? የት ለመድረስ?

አገራዊ ራዕይና ግብን በሚመለከት ለአብነት ቻይና

“The firmly believe that the goal of bringing about a moderately prosperous society in all respects can be achieved by 2021, when the CPC celebrates its centenary; the goal of building China in to a modern socialist country that is prosperous, strong, democratic, culturally advanced and harmonious can be achieved by 2049, when the People’s Republic of China marks its centenary; and the Dream of the Rejuvenation of the Chinese nation will then be realized.” የደመቁና የተሰመረባቸውን ቃላት ለምን? እንዴት? በምን? መቼ? በማን? የሚሉ ሕዝባዊና አገራዊ ጥያቄዎችን ትርጉም ባለው መንገድ ያስቀመጠ፣ ተያያዥና ተመጋጋቢ ተግባራትን በግልጽ ያሠፈረ፣ በፕሮፐጋንዳ ቃላት ያልተሸፈነና ግልጽ ሐሳብ የያዘ፣ በአሳማኝ ጭብጦች የተደገፈ፣ እንኳን ለዜጎቿ ለእኛ ቻይናን ለመረዳትና ለመገንዘብ ያስቻለ እንደሆነ ግልጽ ይመስለኛል፡፡

እኛ ራዕይ ብለን ያስቀመጥነውን ስንመለከት ምን ያህል በአስተሳሰብ ኃላ እንደ ቀረንና በሐሳብ ደሃ እንደሆንን አመላካች ነው፡፡ በሌላ በኩል ከፕሮፐጋንዳ ይልቅ ግልጽ፣ ተያያዥና ሁሉን የሚያቅፍ ብሎም ትውልድ ተሻጋሪ የሆነ ጽንሰ ሐሳብ የያዘ ነው፡፡ የእኛ ግን ከጽንሰ ሐሳባዊ ትስስር ይልቅ ፕሮፐጋንዳዊ ቃላት የሚበዙበት፣ እንኳን ትውልድ የሚሻገር ሊሆን ራዕይና ግብ የተምታታብን ስለመሆናችን ብዙ ጥናትና ምርምር አይጠይቅም፡፡

ከዚህ ባሻገር የአገራችን ብሔራዊ ጣቢያ በየዕለቱ የሚለው፣ መሪዎች በየዕለቱ የሚያስተጋቡት፣ ምሁራን ዘወትር የሚጽፉበት፣ የሚመራመሩበት፣ ሁለንተናዊ ልዩነቶችን መሸከም የሚችል፣ አገር እንደ አገር፣ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ያለ ልዩነት በባለቤትነት ስሜት ይዞ የሚያነሳው የጋራ የሆነ ትርጉም ያለው ሐሳብን ከጽንሰ ሐሳባዊ ጥልቅ አገራዊና ሕዝባዊ እሳቤ ጋር የያዘ ራዕይ የለንም፡፡ ለነገሩ ራዕይ ሳይኖር እንዴት ይገለጻል?

ነገር ግን እንደ አገር ጠቅለል ያለ ራዕይ ባይኖርም (በድጋሚ ራዕይ ተብሎ የተገለጸው ግብ – ከግብም ቢሆን የአጭር ጊዜ ግብ እንጂ ራዕይ ፈጽሞ ሊሆን ስለማይችል) ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና የተለያዩ የመንግሥት አካላት ራዕይ፣ ተልዕኮ በማለት የሚገልጹትና የለጠፉትን ስንመለከት፡፡

ጽንሰ ሐሳባዊ መዘበራረቅ

በርካታ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ራዕይ ብለው የሚያስቀምጡት ሥራቸውን ነው፡፡ ለአብነት፣የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ራዕይ ‹‹ጠቅላይ ሚኒስትሩና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሕገ መንግሥታዊ ተልዕኳቸውን በብቃት ተወጥተው ማየት፤››

ይህ ማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ኃላፊነታቸው፣ ግዴታቸውና ሥራቸው በራሱ ራዕያቸው መሆኑ ነው፡፡ እንዴት ነው ሥራቸው ራዕይ ሊሆን የሚችለው?

እንዲህ ዓይነት ክፍተቶች በበርካታ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት አካላት የሚታይ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲህ ከሆነ እንዴት ነው እሱ የሚሰበስባቸው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የጠራ፣ ግልጽና ተመጋጋቢ የሆነ ራዕይ ማዘጋጀት የሚችሉት? የአገራችን ሥርዓት ራስ እንዲህ ከሆነ ከሌላው ምን ይጠበቃል? ይህ ጽሕፈት ቤት እንዲህ ከሆነ እንደ አገር ራዕይ እንደሌለን ከዚህ በላይ ምን ማስረጃ ይኖር ይሆን?

የይዘት አቀማመጥ ጥራት መጓደል

በርካታ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና የተለያዩ የመንግሥት አካላት ራዕይና ግብን ቀላቅለው፣ ራዕይን ባለማስቀመጥ ግባቸውን ራዕይ ብለው ይገልጻሉ፡፡

በጽንሰ ሐሳብ ደረጃ የጊዜ ገደብ ተቀምጦ የሚገልጹ አካላት በሙሉ እንዲህ ያለ ክፍተት የሚታይባቸው ናቸው፡፡

የኢፌዴሪ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ራዕይ፣ ‹‹በ 2015 ዓ.ም. ሙሉ ለሙሉ የሕዝብ አመኔታ የተቸረው ፍርድ ቤት ሆኖ ማየት፤››

የኢፌዴሪ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ራዕይ፣ በ 2017 ዓ.ም. ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ ሆኖ ማየት፤››

(በጣም የሚያሳዝነው ‹ራዕይ› ተብሎ ራሱ የተገለጸውን እንዳለ ብንቀበል ከእነ ክፍተቱ የአገሪቱ አጠቃላይ ‹ራዕይ› ‹‹በ 2012 – 2015 ዓ.ም. መካከለኛ ገቢ›› ሲል ይህ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ግን ‹በ 2017 ዓ.ም.› ብሎ የራሱን ‹ራዕይ› ያስቀምጣል፡፡ አንድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከአጠቃላይ አገሪቱ ራዕይ በላይ ጊዜ ካስቀመጠ ይህ በራሱ ትርጉም ያለው፣ ጥልቅ፣ ሰፊ፣ ተናባቢ፣ ወጥና ተመጋጋቢ የሆነ አገራዊ ራዕይና ግብ እንደሌለ ተጨባጭ ማስረጃ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ከአጠቃላይ አገራዊ ራዕይ በመነሣት የድርሻቸውን መውሰድ እንዳለባቸው ግድ የሚለውን መርህ በእጅጉ የሳተ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡)

በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ የጊዜ ገደብ ያለው ነገር ግብ እንጂ ራዕይ ሊሆን አይችልም፡፡ ራዕይ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ፣ ትውልድ ተሻጋሪና ረቂቅ የዘውትር ሥራና የማይቀያየር መሆኑን መዘንጋት የማያሻ ይሆናል፡፡

እነዚህ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ከጠቀሱት ዓመተ ምሕረት በኋላ ማሳካት የሚፈልጉት ምንድነው? ሥራ ያቆማሉ ማለት ነው? ለምንድነው በጠቀሱት ዓመተ ምሕረት ላይ ማሳካት ሚፈልጉትን የጠቀሱት? የት ለመድረስ? ለምን?

የአድማስ ጥበት

ራዕይ ማለት እጅግ በጣም የረዥም ጊዜና ዘመን የማይጥለው፣ ዘመንን መዋጀትና ከዘመን ጋር መራመድ የሚችል፣ ትናንትን ከዛሬ፣ ዛሬን ከነገ ጋር ማገናኘት የሚችል የእሳቤ ውጤት የሆነ ትርጉም ያለው ሐሳብ ስብስብ ነው፡፡ ራዕይ በባህሪው አይቀየርም፣ አይለዋወጥም፡፡ ምክንያቱም ማዕቀፉ የረዥም ጊዜ ስለሆነ ግብ በአንፃሩ በየጊዜው በጊዜና በመጠን፣ እንዲሁም በሥራ መለኪያዎች በየጊዜው እየተለዋወጠ ይሄዳል፡፡ ዓላማ እንዳለው ተልዕኮ የሚወሰን መሆኑ ግልጽ ጽንሰ ሐሳባዊ መነሻ ቢሆንም፣ በአገራችን ግን ይህን ጽንሰ ሐሳባዊ መሠረት ሳይዙ ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡

ቢያንስ እንኳን እንዴት ራዕይን በማስቀመጥ ከአፍሪካ መውጣት ያቅተናል? እንዴት አድማሳችን ዓለም አቀፍ መሆን አይችልም? እንዴት ራዕያችን እጅግ የጠበበና ትውልድ የማይሻገር ይሆናል?

የኢፌዴሪ ባህልና ቱሪዝም

ራዕይ፣ ‹‹በኢትዮጵያ በ 2012 ዓ.ም ባህላዊ ሀብቶቿና የተፈጥሮ መስህቦቿ ለምተው በቱሪዝም መዳረሻነት ከመጀመርያዎቹ አምስት የአፍሪካ አገሮች አንዷ እንድትሆን ማድረግ፤››

ከላይ የተጠቀሱት አካላት ለምን አድማሳቸው ጠባብ ሆነ? ለምን ግብና ራዕይን መለየት አቃታቸው? ራዕይስ ለእነሱ ምንድነው? ዕውን የራዕይ ምንነት ገብቷቸዋል? በነጣላ የእነሱ እንደዚህ መሆን የአንዳንዶች ደግሞ ከዓለም አቀፍ ጋር ተያይዞ መቅረብና አድማሳቸው ዓለም አቀፋዊ መሆን፣ እንደ አገር በራዕይ ላይ የጠራ ግልጽ የሆነ መግባባት እንደሌለ ማሳያ አይደለምን?

እንደ አገር የራዕይ አልባነትና መደነባበር ውስጥ እንዳለን ከዚህ በላይ ምን ማሳያ ይኖር ይሆን? አንዳንዱ ራዕዩ በአፍሪካ የታጠረ፣ አንዳንዱ ሥራውን ራዕዩ ያደረገ፣ አንዳንዱ ከአገሪቱ ‹ራዕይ› በላይ፣ አንዳንዱ ደግሞ በታች ‹ራዕያቸውን› ያደረጉ

መሆናቸው (ከ 2015 ዓ.ም. በፊትና በኃላ)፣ አንዳንዱ ግቡን ራዕይ ያደረገ፣ አንዳንዱ ተልዕኮውን ሥራው ያደረገ፣ . . . መሆኑ አገራችን ወዴት ነው እየሄደች ያለችው? ምን ራዕይ ይዘን ነው እየተጓዝን ያለነው? እስከ ዛሬ ይህ ክፍተት ለምን አልታየም?

የቅደም ተከተልና ወጥነት ያለው አቀማመጥ አለመኖር

በርካታ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችም ሆኑ የመንግሥት አካላት ራዕይ፣ ግብ፣ ዓላማ፣ ተልዕኮ፣ እሴት (Deductive መንገድ) አሊያም እሴት – ተልዕኮ – ዓላማ – ግብ – ራዕይ (Inductive መንገድ) በማለት ወጥነት ባለው ሁኔታ ማስቀመጥ ሲገባቸው፣ እጅግ በተዘበራረቀና ወጥነት የሌለው አንዳንዶች ራዕያቸውን ከተልዕኮ በታች ሲያደርጉ፣ ለአብነት የኢፌዴሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተልዕኮን አስቀድሞ ራዕይን ከታች እሴትን ከታች በማድረግ ሲገልጽ፣ ሌሎች በአንፃሩ ራዕይን ከላይ ከዚያ ተልዕኮ፣ እንዲሁም እሴትን ይገልጻሉ፡፡ በአንዳንዶች እንደ ገቢዎች ያሉ ደግሞ ስትራቴጂ የሚል ጨምረው ይታያሉ፡፡

ተመጋጋቢነትና ተደራሽነትን ከባለቤትነት ጋር የመያዝ ክፍተት

ከላይ የተገለጹትም ሆነ ያልተገለጹ ሌሎች አካላት ራዕይ፣ ግብና ተልዕኳቸው ሕዝብ እንደ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ በራሳቸው በመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች በራሱ የማይቀነቀን፣ በባለቤትነት ስሜት የማይነሳ፣ ብሎም ብሔራዊ መግባባትን፣ ብሔራዊ መንፈስና ሕዝባዊ መነሳሳትን ያልፈጠረ መሆኑ በአደባባይ የሚታይ ነው፡፡

ምናልባትም አካላቶቹ ሕዝባዊ የባለቤትነት ስሜትን መፍጠር ቢችሉ ኖሮ ክፍተቶችን ለማየት የሚያስችላቸው ይሆን አልነበርን? ክፍተቶቹስ አይደሉ ሕዝባዊ የባለቤትነት ስሜትና ብሔራዊ መግባባት እንዳይኖር ያደረጉት?

ክፍተቱም ሕዝብ ራሱም ቢሆን ገዥዎችን ለምንድነው የምትመሩን? የት ለመድረስ? ለምን? ተፎካካሪዎችን ለምንድነው እንድንመርጣችሁ የምትፈልጉት? የት ልታደርሱን? ለምን? አገራዊ ራዕይ – አገራዊ ግብ የታላችሁ? የፓርቲና የአገር ራዕይና ግባችሁን ለይታችሁ ንገሩን? የእናንተ ፓርቲ የታል? መሪ ብትሆኑስ ለአገራችን የያዛችሁት የታል? ብሎ ትርጉም ያለው ጥያቄ አለመጠየቁ፣ ጋዜጠኞችና ምሁራን በዚህ ላይ ሰፊ ሥራ አለመሥራታቸው፣ ክፍተቱ ክፍተት ከመሆን ባሻገር ክፍተቱን እንደ ክፍተት አለመረዳታችን የሁላችንም የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ደረጃ ማሳያ ይመስለኛል፡፡

በርካታ በአገራችን በተለያዩ ጊዜያት የወጡና ለመተግበር የተሞከሩ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ስትራቴጂዎችና ሪፎርሞች በሌሎች አገሮች ስኬታማ ከመሆናቸውም በላይ በጽንሰ ሐሳብ የተሟሉ ሆነው ሳለ፣ በአገራችን ግን የሚፈለገውን ውጤት ሳያመጡ ቀርተዋል፡፡ ይህም ተግባራዊ ሲደረጉ ውጤታማ ካልሆኑባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ከአመጣጣቸው፣ ከአቀራረፃቸው፣ ከአቀራረፅ ሒደታቸው፣ ከትግበራቸው አንፃር አገራዊ ማዕቀፍን ትርጉም ባለው መልኩ መነሻና መዳረሻ የማድረግ፣ ብሎም ለአገራዊ ማዕቀፍ ምሰሶ ከሆኑ አገራዊ ራዕይ፣ አገራዊ ግብ፣ አገራዊ ዓላማና አገራዊ ተልዕኮ ጋር ትርጉም ባለው መንገድ አለመተሳሰራቸው ነው፡፡ ስለሆነም ውጤታማ መሆን አልቻልንም፡፡ ልንሆን አለመቻላችን ብዙ አያስገርምም፡፡ ሊያስገርም የሚችለው ውጤታማ ብንሆን ነበር፡፡ ከአሁን በኃላም ቢሆን ይህን ክፍተት ካላረምን ጊዜ ያልፋል፣ ሀብት ይባክናል እንጂ መቼም ቢሆን መሠረታዊ ለውጥ አናመጣም፡፡

የቅርብ ጊዜ ጠንካራ ወዳጃችን ቻይና “Achieving Rejuvenation is the Dream of the Chinese People” ሲኖራት በሌላ በኩል፣ “The Chinese Dream is a Dream of the Country, the Nation as well as all Chinese Individuals” መሆኑን የእንቅስቃሴያቸው መነሻና መዳረሻ አድርገው በሁለንተናዊ መንገድ እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡

ስለሆነም “What is our dream of the country, the Nation as well as all Ethiopian individuals?” ዕውን አለን? ምን? ለምን? እንደሌለን የታወቀ ነው፡፡ ቢኖረን እያንዳንዱ ዜጋ ባቀነቀነው ነበር፡፡ መጽሐፍ ‹ራዕይ የሌለው ሕዝብ ይጠፋል› እንዲል፣ ዜጋ በዜጋነቱ የሚያቀነቅነው ነገር ከሌለ ዜጋነት በራሱ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ቢገባ እንደምን የሚያስደንቅ ይሆናል? ፈጣሪ አገራችን ነፃ ፈቃድን የሁሉ ነገር ማዕከል ወደሚያደርግ የአሳቤ ሒደት ትገባ ዘንድ ይርዳን!

ከአዘጋጁ፡– ጸሐፊው ሽክም የበዛበት ትውልድ 2009 እና የምሥራቃዊት ኮከብ 2010 መጻሕፍት አዘጋጅ ናቸው፡፡
ጽሑፉ የጸሐፊውን አመለካከት ብቻ የሚያንፀባርቅ ሲሆን፣ ጸሐፊውን በኢሜይል

አድራሻቸው tsegazeab17@yahoo.com ማግኘት ይቻላል፡፡